4. Certified Minutes of the Annual General Meeting held on 14 September 2023 confirming the increased Bank’s authorized share capital to ETB 15,000,000,000.

## የእናት ባንክ አክሲዮን ማኅበር

## የባለአክሲዮኖች 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ

## ቃለ-ጉባዔ

1. ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

    1.1 ቦታ፡ - ኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል የመሰብሰቢያ አዳራሽ

    1.2 ቀን፡ - መስከረም 03 ቀን 2016 ዓ.ም.

    1.3 ሰዓት፡ - ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6:00 ሰዓት

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በንግድ ሕግ መሰረት ከጉባዔው ዕለት ሃያ አራት ቀናት አስቀድሞ ነሐሴ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣው የሪፖርተር ጋዜጣ እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጥሪ ተደርጓል።

3. ድምጽ ቆጣሪዎች ፣ፀሐፊ እና በጉባኤው የተገኙ ዳይሬክተሮች እና ታዛቢዎች

ሀ. የጉባኤው ድምፅ ቆጣሪዎች እና ፀሐፊ

ጉባኤውን ለመጀመር በንግድ ህጉ አንቀጽ 380(1) በሚደነግገው መሰረት በጉባኤው ባለአክሲዮንነት ወይም ወኪልነት ከተገኙ እና ፈቃደኛ ከሆኑት 5 ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች (1. ወ/ሮ ሙሉ ደረጄ 2. ወ/ሮ ማህደር ጫኔ 3. አቶ ሚሊዮን አማረ 4. ወ/ሮ አበቡ ካህሰ 5. አቶ አቶ ጌትነት ዳምጤ) መካከል በተደረገው ስምምነት መሰረት ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘረው የጉባኤው ድምፅ ቆጣሪ ሆነው ተመርጠዋል። እንዲሁም የማህበሩ ፀሀፊ የጉባኤው ፀሐፊ ሆነው ተሰይመዋል።

| ተ.ቁ | ስም | የተወካይ ስም |
|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ሙሉ ደረጄ | አቶ ያረጋል ደረጄ |
| 2. | አቶ ጌትነት ዳምጤ | |
| 3. | ወ/ሮ ማህደር ጫኔ | |

ለ. በጉባዔው የተገኙ የቦርድ ዳይሬክተሮች፣

| ተ/ቁ | ሙሉ ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ፍሬሕይወት ወርቁ በየነ | ሰብሳቢ |
| 2 | አቶ ሀብቱ ድምፁ ወረስ | ም/ሰብሳቢ |
| 3 | ወ/ሮ ሮማን ለገሰ ወ/ጊዮርጊስ | አባል |
| 4 | አቶ ኢታና አያና ለታ | አባል |
| 5 | ወ/ሮ ሽታዬ ሁሴን አህመድ | አባል |
| 6 | አቶ ኢዮቤድ ጥበቡ ልሳነወርቅ | አባል |
| 7 | ረ/ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ውሂብ ወ/ማርያም | አባል |
| 8 | ወ/ሮ ይርገዱ በጋሻው ሀብተየስ | አባል |
| 9 | ወ/ሮ አዲስ ዘለቃው በለጠ | አባል |
| 10 | ወ/ሮ ንግስት ወ/ስላሴ ገ/ኪሮስ | አባል |
| 11 | አቶ አየነው ውዱ አዛገው | አባል |

ሐ. በጉባኤው ላይ ያልተገኙ የቦርድ ዳይሬክተሮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የለም | |

መ. በጉባዔው የተገኙ ታዛቢዎች

| ተ/ቁ | ሙሉ ስም | የወከሉት ተቋም |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ማስተዋል አምቤ | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| 2 | አቶ ብሩክ አብርሃም | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |
| 3 | ወ/ሮ ትዕግስት አያሌው | የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት |
| 4 | ወ/ሮ የሺወርቅ ንጉሴ | የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት |
| 5 | ወ/ሮ ዘመናዊ መለሰ | የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት |

4. ምልዓተ ጉባዔ፣

4.1 ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 21,337

4.2 ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክሲዮን ብዛት 2,796,747

4.3 በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 341 የያዙት አክሲዮን ብዛት 995,619

4.4 በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 20997 የያዙት አክሲዮን ብዛት 1,801,128

4.5 ለምልዓተ ጉባዔው አስፈላጊ የሆነ የአክሲዮን ብዛት 922,926.51

በንግድ ሕግ አንቀፅ 402 በተደነገገው መሰረት ከአክስዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች 35.6% የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በጉባኤው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሳኔ ለማሳለፍ ስልጣን ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ ጉባኤው ቀጥሏል። የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ 970 ገፅ ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር በአባሪነት ተያይዟል።

## 5. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፣

የጉባኤው ሰብሳቢ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጉባኤውን አጀንዳዎች በንባብ አሰምተዋል።

5.1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፣
5.2. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፣
5.3. የባንኩን የካፒታል እድገት ውሳኔዎች መርምሮ ውሳኔ ማስተላለፍ፣
5.4. የባንኩን ካፒታል ማሳደግ፣
5.5. በአዲሱ ንግድ ህግ መሰረት የተሻሻለው የባንኩን መመስረቻ ፅሑፍ ላይ ተወያይቶ ማፅደቅ፣
5.6. ቃለ ጉባኤውን ማፅደቅ።

## 6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃል

## 6.1 የባንኩን የካፒታል እድገት ውሳኔዎች መርመሮ ውሳኔ ማሳለፍ፣

የጉባኤው ሰብሳቢ ይህ የባለአክሲዮኖች 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተጠራው ባንኩ በታህሳስ 02 ቀን 2008ዓ.ም ባደረገው የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መሰረት የባንኩ ካፒታል እድገት ውሳኔ አፈፃፀም የሚያበቃው በታህሳስ 02 ቀን 2013 ዓ.ም እንደሆነ፤ ከዚህ ቀን በኋላ አክሲዮኖች ለሽያጭ የቀረቡበት መንገድ የህግ ክፍተት ያለበት መሆኑን ለባንኩ በማሳወቅ ባንኩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በመጥራት እርምት እንዲያደርግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳሰቢያ በመስጠቱ መሆኑን ለጉባኤው ገልፀው ከ1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ የባንኩን የካፒታል እድገት በዝርዝር ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርበዋል፤

በዚሁ መሰረት፡-

1. ታህሳስ 02 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገው የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የባንኩ ካፒታል ወደ ብር 2 ቢሊዮን እንዲያድግ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት የባንኩ አክሲዮን ሽያጭና የውሳኔው ተፈፃሚነት የሚያበቃው በታህሳስ 02 ቀን 2013 ዓ.ም ሲሆን ነገር ግን ከታህሳስ 03 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ብዛቱ 1,255,537 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊየን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት) የሆኑ አክሲዮን በብር

1,255,537,000.00 (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ብር) የሆነ የአክሲዮን ሽያጭ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ቀድሞ ሳይወስን መከናወኑን፣

2. ከተሸጠው አክሲዮን ውስጥ ብዛቱ 912,365 (ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ አምስት) በብር 912,365,000.00 (ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ) የሆነ አክሲዮን በነባር ባለአክሲዮኖች፤ ብዛቱ 343,172 (ሶስት መቶ አርባ ሶሶት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት) የሆነ በብር 343,172,000.00 (ሶስት መቶ ሚሊዮን አርባ ሶስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ ብር) የሆነ ደግሞ በአዲስ ባለአክሲዮኖች ፣ ግዥ መፈጸሙን፣

3. እስከ ህዳር 24 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስም የባንኩ የተፈረመ አጠቃላይ ካፒታል ብር 2,796,747,000.00 (ሁለት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) መድረሱን፣

4. ከታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ.ም በኋላ የተሸጡትን አክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው አስቀድሞ ውሳኔ ማስተላለፍ የነበረበት መሆኑን፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች የተከፈለ ካፒታላቸውን ብር 5 ቢሊዮን እንዲያደርሱ ያስተላለፈውን ውሳኔ ለማሳካት ሲባል ቦርዱ በቅን ልቦና አክሲዮኖቹ እንዲሸጡ እና ባንኩ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት እንዲችል እንዲሁም እናት ባንክ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት ከሌሎች ባንኮች ጋር ሳይቀላቀል ህልውናውን አስጠብቆ መቀጠል እንዲችል ለማስቻል የአክሲዮኖች ሽያጭ ሲያደረግ መቆየቱን፣

5. በዚህ ሂደት ውስጥም ባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮኖችን እንዲገዙ ያላሰለሰ ጥሪ ሲያስተላልፍ መቆየቱን፣ ባለአክሲዮኑም የባንኩን ጥሪ ተቀብሎ አዲስ ከተሸጡት በብር 1,255,537,000.00 (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ ብር) የሆኑ አክሲዮኖች ውስጥ መጠናቸው ብር 912,365,000.00 (ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ) የሆኑ አክሲዮኖች ሊገዛ መቻሉን፣ ይህም ነባር ባለአክሲዮኑ ባንኩ የብር 5 ቢሊዮን ካፒታል መስፈርትን ለማሳካት እየተደረገ ላለው ጥረት ቀና ትብብር ያደረገበትና የባንኩ ህልውና እንዲረጋገጥ ያለውን ፍላጎት ያሳየበት መሆኑን፣

6. ይሁን እንጂ ለውጪ በተሸጠው ብር 343,172,000.00 (ሶስት መቶ አርባ ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ) የሆነ አዲስ አክሲዮን ላይ ነባር ባለአክሲዮኑ ቅድሚያ ለመግዛት የቀደምትነት መብት የነበረው ቢሆንም ይህንን ሳይጠብቅ ባንኩ ሽያጩን ያከናወነው ለባንኩ ጥቅም መሆኑን ባለአክሲዮኑ እንዲገነዘብና፣ በዚህም ምክንያት የባለአክሲዮኑ የቀደምትነት መብት በከፊል መገደቡን ጠቅላላ ጉባኤው የተቀበለው መሆኑን ማረጋገጫ እንዲሰጥ በመጠየቅ፤ ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ማሳለፍ እንዲችልም በጠቅላላ ጉባኤ የውጪ ኦዲተር ተደርጎ የተሾመው ታፈሠ፣ ሺሰማ እና አያሌው የተረጋገጠ የኦዲት ሽርክና፣ቻርተርድ ሰርቲፋይድ አካውንታንትስ በቦርዱ በቀረበው ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለጠቅላላ ጉባኤው አስተያየት እንዲሰጥ ጋብዘዋል፣

7. የውጪ ኦዲተሩም በአስተያየቱ ከታህሳስ 03 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አዲስ የተሸጡ አክሲዮኖች የባንኩ አክሲዮን አካል መሆናቸውን ያረጋገጠ መሆኑን ፣ ከተሸጡት አክሲዮኖች ውስጥ ነባር ባለአክሲዮኖች በብር 912,365,000.00 (ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር) አክሲዮኖች ግዥ መሆኑን ፣ በብር

343,172,000.00 (ሶስት መቶ አርባ ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ ብር) የሆነ አክሲዮን ደግሞ ለውጩ ገዥዎች የተሸጠ መሆኑን፣በዚህ የአፈፃፀም ሂደትም ነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ለመግዛት የነበራቸው የቀደምትነት መብት በከፊል የተገደበ መሆኑንና የዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበውን ሪፖርት የሚያረጋግጥ መሆኑን ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው ገልጿል፣

ከዚህ በመቀጠልም የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው በአጀንዳው ላይ እንዲወያይ መድረኩን ክፍት ካደረጉ በኋላ በተካሄደው ውይይት የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በጉባኤው ተሳታፊዎች ተነስተዋል።

በጉባኤው ተሳታፊዎች የተነሱት ጥያቄዎችና አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው፣

- ለውጭ የተሸጡት አክሲዮኖች ለተወሰኑ ገዥዎች ወይም ለህዝብ ክፍት ተደርጎ መሆኑ እንዲብራራ፣ ምክንያቱም የተወሰኑ ሰዎች በባንኩ ላይ የተለየ ተፅእኖ እንዲያሳድሩ እድል እንዳይፈጠር ስጋት በመኖሩ ምክንያት መሆኑን፣
- ከባለአክሲዮኑ ፈቃድ ውጭ አክሲዮን በመሸጥ የተፈጠረውን ህገ ወጥ አካሄድ ባለአክሲዮኑ ህጋዊ የሚያደርግበት አግባብ መኖሩ እንዲብራራ፣
- ቀደም ሲል ባንኩ ባካሄዳቸው ጠቅላላ ጉባኤዎች ባለአክሲዮኑ ሲያነሳቸው የነበሩት ጥያቄዎችና ስጋቶች ባንኩ እንዴት ሊያድግ ይችላል? ፣ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ባንኩ እንዴት አድርጎ ካፒታሉን ወደ ብር 5 ቢሊየን ማሳደግ ይችላል? ባንኩ መመሪያውን ተግባራዊ ካላደረገ የሚኖረው አማራጭ ከሌላ ባንክ ጋር መቀላቀል እንደሚሆን እና ይህም የባንኩን ራዕይ ለማስቀጠል እንደማያስችል የሚያሳስቡ እንደነበሩ፣ ከዚህም በመነሳት ቦርዱ እና የባንኩ ማኔጅመንት ያከናወኑት ውጤታማ ተግባር የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስወቅስ እንዳልሆነ፣
- ባለአክሲዮኑ በሴክተሩ ያለውን ከፍተኛ ውድድር በመገንዘብ የራሱን ባንክ አደጋ ላይ ከሚጥሉ አስተያየቶች በመቆጠብ አጀንዳው ሊያደርግ የሚገባው የባንኩን ካፒታል አሁን ካለው ብር 2.7 ቢሊየን ወደ ብር 5 ቢሊየን ለማድረስ ምን መደረግ አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ መሆኑን፣
- ባንኩ ባካሄደው አዲስ አክሲዮኖችን የመሸጥ ሂደት የተዘለሉ አካሄዶች ቢኖሩም ባንኩን ወደ ፊት ለማስኬድ ነው ወይስ ወደ ኋላ የሚለውን ሀሳብ ማየት እንደሚገባ፣ለተገኘውም ውጤት ከታችኛው የባንኩ ሰራተኛ እስከ ቦርዱ ድረስ ምስጋና ማቅረብ ተገቢ እንደሆነ፣
- አዲስ ከተሸጠው አክሲዮን ውስጥ ለነባር ባለአክሲዮኖች የተሸጠው ከፍ ያለ መሆኑ በራሱ ባለአክሲዮኑ የባንኩ አክሲዮን ተሸጦ የካፒታል መስፈርቱ እንዲሟላ ያለውን ፍላጎት እንደሚያሳይ፣ አሁንም ባለአክሲዮኑ ለቦርዱና ለማኔጅመንቱ አደራ ሊሰጥ የሚገባው ቀሪውን 2.3 ቢሊየን ለማሟላት እንዲሰሩ መሆኑን፣
- ባለፈው የባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ የባንኩ ፕሬዝዳንት ትንሽ ጊዜ ከተሰጣቸው ባንኩን ለመለወጥ እንደሚችሉ በገቡት ቃል መሰረት ላሳዩት ውጤት ምስጋና የሚገባቸው መሆኑን፣አሁንም

የአክሲዮን ሽያጩን በሁሉም ጋዜጣዎች በማውጣት እንዲፋጠን እንዲደረግ እና ባለአክሲዮኑ የባለቤትነት ስሜት እንዲያዳብር ለማበረታታት ጥረት እንዲደረግ የሚያሳስቡ ናቸው።

ከጉባኤው ለተነሱት የማብራሪያ ጥያቄዎች ከመድረኩ በተሰጠው ምላሽ፣

- ባንኩ የሸጣቸው አክሲዮኖች ለተወሰኑ ገዥዎች ብቻ አለመሸጣቸውን እና አክሲዮኖቹ ለህዝብ ክፍት ተደርጎ የተሸጡ መሆናቸውን፣እና
- ባንኩ አክሲዮኖቹን በመሸጡ የደረሰ ጉዳት ባይኖርም አፈፃፀሙ ህግን ተከትሎ ሊከናወን እንደሚገባው የሚታመንበት በመሆኑና ብሔራዊ ባንክም ይህንኑ እድል በመፍቀዱ የእለቱ ስብሰባ መጠራቱን በመጥቀስ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ከዚህም በመነሳት የጉባኤው ሰብሳቢ በአፈፃፀም የታየውን የህግ ክፍተት ለማረም ከታህሳስ 03 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አዲስ የተሸጡት አክሲዮኖች የባንኩ የካፒታል አካል እንዲሆኑ እና የባለአክሲዮኑ የቀድምትነት መብት በከፊል ተገድቦ ለውጪ የተሸጡትንም አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤው መቀበሉን እንዲያረጋግጥ ጠይቀዋል፣ ጠቅላላ ጉባኤውም የዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

## 6.2. የባንኩን ካፒታል ማሳደግ

### 6.2.1 የባንኩ ካፒታል የሚያድግበትን መጠን መወሰን፣

የጉባኤው ሰብሳቢ የባንኩን የካፒታል ማሳደግ አስፈላጊነት በሚመለከት ባቀረቡት ማብራሪያ:-

ሀ. የባንኩን የማበደር አቅም የሚያሳድግ መሆኑን፣
ለ. በባንኩ ሃብት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን አደጋዎች ለመቋቋም የሚረዳ መሆኑን፣እና
መ. ባንኩ ለካፒታል ኢንቨስትመንት ለሚያወጣው ገንዘብ መሸፈኛ ማለትም ለተቀናጀ የባንክ ቴክኖሎጂ እና ሕንፃ ግንባታ ወጪ መሸፈኛ ሊሆን የሚችል መሆኑን ካስረዱ በኋላ የባንኩ ካፒታል ወደ ብር 15,000,000,000.00 (አስራ አምስት ቢሊዮን) እንዲያድግ የውሳኔ ሃሳብ መቅረቡን በመግለጽ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል፣

ጉባኤውም በቀረበው የካፒታል ማሳደግ ውሳኔ ላይ ተወያይቷል።

በውይይቱም፣

- ትልቅ ቦታ ሊደረስ የሚችለው ትልቅ ሀሳብ ይዞ በመነሳት በመሆኑና ባንኩ በብዙዎች ተወዳጅነት ያለው ስለሆነ ከፍተኛ ጥረት ቢጠይቅም የታሰበው የብር 15 ቢሊየን ካፒታል ላይ ለመድረስ እንደሚቻል እንደሚታመንበት፤ እንዲሁም የውጭ ባንኮችም ሊመጡ ስለሚችሉ ካፒታሉን ከፍ ማድረግ ተገቢ እንደሚሆን፣
- ካፒታሉን ወደ ብር 15 ቢሊየን ከፍ ማድረጉ ጥሩ መሆኑን፣ ሆኖም ሽያጩ የድርጊት መርሃ-ግብር ወጥቶለት በየዓመቱ አፈፃፀሙ እየተገመገመ ሊሆን እንደሚገባ፣
- ባንኩን ለማስተዋወቅ ከሚዲያ ጋር የተፈጠረው ግንኙነት ጥሩ መሆኑን፣

- ባንኩን ከሌላ ባንክ ጋር ማዋሃድ እንደ ጥሩ የቢዝነስ እድል የማይታይበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግልጽ እንዲደረግ፣
- ታዋቂ የሆኑ ትልልቅ እናቶችን በመጠቀም ባንኩን ለማስተዋወቅ ያለውን እድል መጠቀም ጥሩ መሆኑን፣
- ባለፈው ጠቅላላ ጉባኤ የተባለው የባንኩን ካፒታል ብር 5 ቢሊየን ለማድረስ እንደሚቻል፣ ካልተሳካ ግን ከሌላ ባንክ ጋር መዋሃድ እንደ አማራጭ እንደሚታይ የተገለጸ ቢሆንም ባንኩ ከዚያ ተነስቶ አሁን ወደ ብር 15 ቢሊየን ካፒታሉን ለማሳደግ ማቀዱ ተስፋ የሚያሳድር መሆኑን፣ እና
- በአሁኑ ጊዜ አክሲዮን መሸጥ ከባድ በመሆኑ መጀመሪያ ወደ 10 ቢሊየን እንዲያድግ በማድረግ ከዚያ በኋላ ወደ ብር 15 ቢሊየን ለማሳደግ ቢሞከር እንደሚሻል፣የሚሉ ጥያቄዎችና እና አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

በጉባኤው ለተነሱት ጥያቄዎችም፣

- ባንኩ የአክሲዮን ሽያጩን የሚያስፈፅመው ምንጊዜም እንደሚያደርገው የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ በዕቅድ በመመራት መሆኑን፣
- ባንኩ ከሌሎች ባንኮች ጋር ለመዋሀድ የሚገደድ ቢሆን ሊኖር የሚችለውን ተፅእኖ በሚመለከት የባንኩ ማኔጅመንት ጥናት ማካሄዱን፣ ከዚህም በመነሳት የባንኩን ራዕይና መሰረተ ሃሳቦች የሚያጠፋ እንዳይሆን ሲባል የባንኩን ካፒታል በማሳደግ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ የሚፈለግበትን ግዴታ ማሟላት የተሻለ አማራጭ ሆኖ መወሰዱን፣እና
- ባንኩ የግድ ከሌላ ባንክ ጋር የሚዋሀድበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ለመደራደርም ሆነ የተሻለ አማራጭ ይዞ ለመገኘት ካፒታሉን በማሳደግ ጠንካራ ሆኖ መገኘት የበለጠ እድል እንደሚፈጥር፣ በተጨማሪም የውጭ ባንኮች ቢመጡ ባንኩ ለሽያጭ የቀረበ አክሲዮን ቢኖረው ጥሩ መሆኑን፣ በመግለጽ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

ከውይይቱም በኋላ ጉባኤው የባንኩ ካፒታል ወደ ብር 15,000,000,000.00 (አስራ አምስት ቢሊዮን) እንዲያድግ በጉባኤው ሰብሳቢ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ ጠቅላላ ጉባኤውም የባንኩ ካፒታል ወደ ብር 15,000,000,000.00 (አስራ አምስት ቢሊዮን) እንዲያድግ በመወሰን በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

### 6.2.2 የባንኩ ካፒታል የሚያድግበትን መንገድ መወሰን ፣

የባንኩን ካፒታል የማሳደጊያ መንገድ በንግድ ሕጉ ከተቀመጡት አማራጮች በመነሳት አዲስ አክሲዮን ለሽያጭ በማቅረብ እንዲሆን የጉባኤው ሰብሳቢ የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤውም የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከመረመረ በኋላ የባንኩ ካፒታል ማሳደጊያ መንገድ አዲስ አክሲዮን በመሸጥ እንዲሆን በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

## 6.2.3 በቀደምትነት መብት አክሲዮን የመግዛት መብት ገደብ ላይ ተወያይቶ መወሰን ፣

የጉባኤው ሰብሳቢ የንግድ ህጉ ባለአክሲዮኖች አዲስ የሚሸጡ አክሲዮኖች ለመግዛት የቀደምትነት መብት እንዳላቸው የሚደነግግ መሆኑን ሆኖም ይህ የባለአክሲዮኖች መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲገደብ የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው መወሰን እንደሚችል፣ ይህንም ለመወሰን የቀደምትነት መብት እንዲቀር ያስፈለገበትን ምክንያት ፣ አዲሶቹን አክሲዮኖች የሚከፋፈሏቸው ባለአክሲዮኖች እና ለያንዳንዳቸው የሚደርሰውን አክሲዮን ብዛት ፣ ለሽያጭ የወጡበትን ዋጋ እና ዋጋው የተወሰነበትን መነሻ የሚገልፅ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የውጪ ኦዲተር ሪፖርት ቀርቦለት ከመረመረ በኋላ እንደሆነ በህግ መቀመጡን ከገለጹ በኋላ የባለአክሲዮኖችን የቀደምትነት መብት በከፊል ለመገደብ ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበውን ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርበዋል፤

በሪፖርቱም ፦

- አዲስ በሚሸጡ አክሲዮኖች ላይ ነባር ባለአክሲዮኖች የሚኖራቸውን የቅድሚያ መብት በከፊል በመገደብ ለውጪ ገዥዎች መሸጡ ያስፈለገበት ምክንያት 1ኛ አዲስ አክሲዮን ለሽያጭ ሲቀርብ በንግድ ህጉ መሰረት በ 5 ዓመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ተሸጦ ማለቅ እንዳለበት በመደንገጉ፣ ሆኖም አሁን ለሽያጭ የሚቀርበው አክሲዮን በመጠን ከፍ ያለና ለነባር ባለአክሲዮኖች ብቻ ተሸጦ ሊያልቅ የማይችል በመሆኑ፣ 2ኛ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች የተከፈለ ካፒታላቸውን ብር 5 ቢሊዮን እንዲያደርሱ ያስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ከ3ት ዓመት በታች የቀረው በመሆኑ፣ እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 2,796,747,000.00 (ሁለት ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ስድስት ሚሊዮን ሳባት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ብር) በመሆኑ ባንኩ የተጣለበትን መስፈርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሳካት አዲስ አክሲዮኖችን ለነባር ባለክሲዮኖች ከመሸጥ ባለፈ ለውጪ ገዥዎች ማቅረቡ አስፈላጊ በመሆኑ፣ 3ኛ በሀገር ደረጃ በባንክ ኢንዱስትሪው የውጭ ባንኮች መሳተፍ የሚችሉበት የህግ ማዕቀፍ የፀደቀ ሲሆን እነዚህ ባንኮች ለወደፊት በባንካችን አክሲዮን ገዝተው ባለቤት እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ ካፒታሉን በማሳደግ ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት እንዲያስችል የባንኩን ካፒታል ከባለአክሲዮኖች ባለፈ ለሌሎች እንዲሸጥ መፍቀድ አስፈላጊ መሆኑ እንደ ዋና ዋና ምክንያቶች መታየታቸውን ገልፀዋል ፣
- አዲሶቹን አክሲዮኖች የሚከፋፈሏቸውም እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አክሲዮን በመግዛት የባንኩ ነባር ባለአክሲዮን የሆኑ ባለአክሲዮኖች መሆናቸውን፣ የባንኩን ካፒታል ወደ ብር 15 ቢሊዮን ለማሳደግ ለሽያጭ የሚቀርበው አክሲዮን በብር 12,203,253,000.00 (አስራ ሁለት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ብር) መሆኑን ከዚህ ውስጥ እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም አክሲዮን በመግዛት የባንኩ ነባር ባለአክሲዮን የሆኑ ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ለመግዛት ያላቸውን የቅድሚያ መብት በከፊል በመገደብ 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የሚሆነውን አክሲዮን ማለትም በብር 3,050,813,250.00 (ሶስት ቢሊዮን ሃምሳ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) የሆነውን አክሲዮን እንዲገዙ እንዲደለደልላቸው፣ ቀሪው 75% (ሰባ አምስት በመቶ) በብር 9,152,439,750.00 (ዘጠኝ ቢሊዮን

አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) የሆነው አክሲዮን ደግሞ ለውጪ ገዥዎች ለሽያጭ እንዲቀርብ፣

- የንግድ ህጉ አንቀጽ 247 አነስተኛው የአክሲዮን ዋጋ ከብር 100 በታች መሆን የለበትም በሚል ያስቀመጠውን ድንጋጌ መነሻ በማድረግ የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ የቀረበው የአክሲዮን ሽያጭ የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ) እንደሚሆን በመግለጽ የቦርዱን ሪፖርት አቅርበዋል ፣

በመቀጠልም የጉባኤው ሰብሳቢ የውጪ ኦዲተር የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት ትክክለኛነት ያረጋገጠበትን ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው እንዲያቀርብ ጋብዘዋል፣

የውጪ ኦዲተሩም ባለአክሲዮኖች በቀደምትነት መብት አክሲዮን ለመግዛት ያላቸው መብት በከፊል ለመገደብ ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበው ሪፖርት ህጉን ተከትሎ የቀረበ መሆኑን፣ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ትክክለኛነትም ለጠቅላላ ጉባኤው ማረጋገጫ እንደሚሰጥና ጠቅላላ ጉባኤው በቀረበው ሪፖረት መሰረት ማፅደቅ እንደሚችል ለጠቅላላ ጉባኤው ገልጿል፡፡

ከዚህም በመነሳት የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ እንዲወያይ መድረኩን ክፍት ካደረጉ በኋላ በጉባኤው ተሳታፊዎች በኩል፣

- አዲሶቹ አክሲዮኖች ሲሸጡ አንድ ገዢ ለመግዛት የሚችለው የአክሲዮን መጠን ገደብ ያለው መሆኑ እንዲገለጽ፣እና
- ለነባር ባለአክሲዮኖች ከተደለደለው 25% (ሀያ አምስት በመቶ) ሌላ ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት የሚፈልጉ ባለአክሲዮኖች ቢኖሩ ለመግዛት የሚችሉ መሆኑ እንዲገለጽ፣በማሳሰብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

በጉባኤው ተሳታፊዎች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከመድረኩ በተሰጠው ምላሽ፣

- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ህግ መሰረት አንድ ባለአክሲዮን በባንኩ ውስጥ ሊኖረው የሚገባው ከፍተኛው የአክሲዮን ድርሻ ከጠቅላላው ከተፈረመው የባንኩ ካፒታል 5% ( ሀያ አምስት በመቶ) መብለጥ የሌለበት መሆኑን ፣ ባንኩም ህጉን አስጠብቆ የሚሰራ መሆኑን ፣እና
- እንዲሁም ለነባር ባለአክሲዮኖች ከተወሰነው 25% (ሀያ አምስት በመቶ) አክሲዮን ውስጥ ከተደለደለላቸው አክሲዮን በላይ ለመግዛት የሚፈልጉ ባለአክሲዮኖች ለውጭ ከቀረበው አክሲዮን ውስጥ ሌላ ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ ተገልጿል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤውም አዲስ በሚሸጡት አክሲዮኖች የቀደምትነት መብቱን በከፊል ለመገደብ የቀረበውን ሪፖርት መርምሮ የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል፡-

- ጠቅላላ ጉባኤው አዲስ በሚሸጡት አክሲዮኖች የባለአክሲዮኑ የቀድምትነት መብት በከፊል እንዲገደብ በሙሉ ድምፅ በማረጋገጥ አዲስ ለሽያጭ ከሚቀርበው በብር 12,203,253,000.00

Documents Authentication & Registration Service Branch
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

(አስራ ሁለት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሶስት ሺህ ብር) የሆነ አክሲዮን ውስጥ እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የባንኩ ነባር ባለአክሲዮን ለሆኑ ባለአክሲዮኖች 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የሚሆነውን አክሲዮን ማለትም በብር 3,050,813,250.00 (ሶስት ቢሊዮን ሃምሳ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) የሆነውን አክሲዮን እንዲገዙ እንዲደለደልላቸው፣ቀሪው 75% (ሰባ አምስት በመቶ) በብር 9,152,439,750.00 (ዘጠኝ ቢሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) የሆነው አክሲዮን ደግሞ ለውጪ ገዥዎች ለሽያጭ እንዲቀርብ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

- የአንዱ አክሲዮን መሸጫ ዋጋም ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ) እንዲሆን በሙሉ ፀድቋል፡፡

### 6.2.4 በቀደምትነት መብት አክሲዮን የመግዛት ጊዜ ገደብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

በንግድ ህጉ አንቀጽ 454 መሰረት ለነባር ባለአክሲዮን በቀደምትነት መብት አክሲዮን የመግዛት መብት የሚሰጠው ጊዜ አዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ከሰላሳ ቀናት ያላነሰ መሆን እንዳለበት መመላከቱን የጉባኤው ሰብሳቢ ለጠቅላላ ጉባኤው በመግለፅ እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አክሲዮን የገዙ የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች የ2ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፀድቆ በፌዴራል ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት ከተመዘገበ እንዲሁም ቀድሞ ለሽያጭ ከወጣውና ከተፈረመው ካፒታል ያልተሰበሰበው ብር 258,498,819.17 (ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ17/100) ተከፍሎ ከተጠናቀቀ በኋላ ባንኩ አዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በቀደምትነት መብታቸው ተጠቅመው እንዲገዙ የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፣

የጉባኤው ሰብሳቢ ባቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ ላይ ጉባኤው ባካሄደው ውይይት፣

- ነባር ባለአክሲዮኖች የተደለደለላቸውን አክሲዮን በ30 ተከታታይ ቀናት እንዲገዙ የተቀመጠው ገደብ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ እና 60 ወይም 90 ቀናት እንዲሆን በማሳሰብ ከጉባኤው ተሳታፊዎች ጥያቄ ቀርቧል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤውም በዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ ነባር ባለአክሲዮኖች የ2ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፀድቆ በፌዴራል ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት ከተመዘገበ እንዲሁም ቀድሞ ለሽያጭ ከወጣውና ከተፈረመው ካፒታል ያልተሰበሰበው ብር 258,498,819.17 (ሁለት መቶ ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከ17/100) ተከፍሎ ከተጠናቀቀ በኋላ ባንኩ አዲስ አክሲዮኖች ለሽያጭ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ በቀደምትነት መብታቸው ተጠቅመው እንዲገዙ በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡

6.2.5 በቀደምትነት መብት ያልተገዙ አክሲዮኖችን ለውጪ ለመሸጥ ተወያይቶ መወሰን ፤

ነባር ባለአክሲዮኖች አክሲዮን ለሽያጭ በቀረበ በሶስት ወራት ውስጥ የተደለደለላቸውን አዲስ አክሲዮን በቀደምትነት መብታቸው ተጠቅመው ያልገዙ እንደሆነ ያልተገዙትን አክሲዮኖች ሌሎች ነባር ባለአክሲዮኖች ለመግዛት ጥያቄ አቅርበው ከሆነ ለነርሱ እንዲደለደል ፤ እነርሱም ባንኩ አክሲዮኑን እንዲገዙ ዳግም ለሽያጭ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ካልገዙ ለውጪ እንዲሸጥ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲወስን የዳይሬክተሮች ቦርድ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረቡን በመግለጽ የጉባኤው ሰብሳቢ ለጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ አቅርበዋል፤

ጠቅላላ ጉባኤውም የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በመቀበል ባለአክሲዮኖች የተደለደለላቸውን አክሲዮን በሶስት ወራት ውስጥ እንዲገዙ፤ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልገዙ ግን ከሌሎች ነባር ባለአክሲዮኖች ውስጥ ተጨማሪ ለመግዛት የጠየቁ ካሉ እንዲገዙ የ30 ቀን እድል እንዲሰጣቸውና እነርሱም ካልገዙ ለውጪ እንዲሸጥ በሙሉ ድምፅ ወስኗል።

6.2.6 አዲስ የሚገዛ አክሲዮን አከፋፈል ሁኔታ፤

የጉባኤው ሰብሳቢ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ዝቅተኛ የተከፈለ ካፒታላቸውን ብር 5 ቢሊዮን በአምስት ዓመት ውስጥ እንዲያደርሱ ያስተላለፈው ውሳኔ የቀረው ጊዜ ከሶስት ዓመት በታች መሆኑን በመግለጽ ባንኩ ይህንኑ መስፈርት ማሳካት እንዲያስችለው አዲስ ከሚሸጠው አክሲዮን የአክሲዮን ግዥ የሚፈፅሙ ነባርና አዲስ ገዥዎች ከሚገዙት አክሲዮን 50% (ሃምሳ በመቶ) ወዲያውኑ እንዲከፍሉ ቀሪውን ደግሞ በሶስት ዓመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍለው እንዲጨርሱ የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፤

በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ጉባኤው ባካሄደው ውይይት፤

- ነባር ባለአክሲዮኖች የተደለደለላቸውን አክሲዮን ሲገዙ ወዲያውኑ እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው 25% (ሀያ አምስት በመቶ) እንዲሆን እና ቀሪውን 75% (ሰባ አምስት በመቶ) በ3 ዓመት ከፍለው እንዲጨርሱ እንዲደረግ በጉባኤው ተሳታፊዎች ጥያቄ ቀርቧል።

ጠቅላላ ጉባኤውም የአክሲዮን ግዥ የሚፈፅሙ ነባር ባለአክሲዮኖች ከሚገዙት አክሲዮን 25% (ሀያ አምስት በመቶ) ወዲያውኑ እንዲከፍሉ፤ ቀሪውን ደግሞ በ3 ዓመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍለው እንዲጨርሱ፤ አዲስ አክሲዮን በመግዛት የባንኩ ባለአክሲዮን የሚሆኑት ግን ከሚገዙት አክሲዮን 50% (ሃምሳ በመቶ) ወዲያውኑ እንዲከፍሉ ቀሪውን ደግሞ በ3 ዓመት ጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍለው እንዲጨርሱ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል።

6.2.7 አዲስ የሚገዛው ዝቅተኛው አክሲዮን ብዛት፤

የባንኩ አንድ የአክሲዮን መሸጫ ዋጋ በብር 1,000.00 (አንድ ሺህ) ሆኖ አዲስ አክሲዮን በመግዛት ባለአክሲዮን የሚሆነው ሰው የሚገዛው ዝቅተኛው የአክሲዮን መጠን በቁጥር 25(ሃያ አምስት) እንዲሆን

ሆኖም ግን አንዴ የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ ሰው በማንኛውም ጊዜ ዝቅተኛውን በቁጥር 1(አንድ) አክሲዮን መግዛት እንዲችል የጉባኤው ሰብሳቢ የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል ፤

ጠቅላላ ጉባኤውም የአንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ) ሆኖ አዲስ አክሲዮን በመግዛት ባለአክሲዮን የሚሆነው ሰው የሚገዛው ዝቅተኛው የአክሲዮን መጠን በቁጥር 25 እንዲሆን እንዲሁም አንዴ ባለአክሲዮን የሆነ ባለአክሲዮን ዝቅተኛውን በቁጥር ከአንድ አክሲዮን ጀምሮ መግዛት እንደሚችል በመወሰን በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡

## 6.2.8 አክሲዮን ሲገዛ ስለሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣

አዲስ አክሲዮን ሲገዛ በተገዛው አክሲዮን መጠን ላይ 5% (አምስት በመቶ) የሚሰላ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል በ1ኛ የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መወሰኑን፣ ሆኖም የአገልግሎት ክፍያው አክሲዮን ገዝተው የባንኩ ባለአክሲዮን የሆኑ ባለአክሲዮኖችን አዲስ አክሲዮን እንዲገዙ የማያበረታታ መሆኑን፣ በመሆኑም የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖችና አዲሱን አክሲዮን ገዝተው ባለአክሲዮን የሆኑ ሰዎች ተጨማሪ አክሲዮን እንዲገዙ ለማበረታታት ሲባል ተጨማሪ አክሲዮን ሲገዙ 5% (አምስት በመቶ) የአገልግሎት ክፍያ ተግባራዊ መደረጉ እንዲቀር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አክሲዮን በመግዛት የባንኩ ባለአክሲዮን ለመሆን የሚፈልጉ ግን 5% (አምስት በመቶ) የአገልግሎት ክፍያ በሚገዙት አክሲዮን መጠን ላይ እንዲከፈል በጉባኤው ሰብሳቢ የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፣

ጠቅላላ ጉባኤውም የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች እና አዲሱን አክሲዮን ገዝተው ባለአክሲዮን የሆኑ ሰዎች ተጨማሪ አክሲዮን ሲገዙ 5% (አምስት በመቶ) የአገልግሎት ክፍያ እንዳይከፍሉ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አክሲዮን በመግዛት የባንኩ ባለአክሲዮን ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ግን በሚገዛው አክሲዮን መጠን ላይ 5% (አምስት በመቶ) የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል በመወሰን በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

## 6.2.9 ከአክሲዮን ሽያጭ ጋር በተገናኘ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን ስለመስጠት፣

የዳይሬክተሮች ቦርድ አዲስ የሚሸጡ አክሲዮኖች ሽያጭን እንዲያስፈፅም ሙሉ ስልጣን እንዲሰጠው የጉባኤው ሰብሳቢ የውሳኔ ሃሳብ አቀርበዋል ፤

ጠቅላላ ጉባኤውም የዳይሬክተሮች ቦርዱ አዲስ የሚሸጡ አክሲዮኖችን ሽያጭ እንዲያስፈፅም በመወሰን የቀረበውን የውሳኔ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

## 6.3 የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ ስለማሻሻል

ከአዲሱ የንግድ ህግ አንፃር የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ ማሻሻል ማስፈለጉን እንዲሁም ተጨማሪ ስልጣኖችን በመመስረቻ ፅሑፉ መስጠት ማስፈለጉን የጉባኤው ሰብሳቢ ለጉባኤው በማስረዳት የተሻሻለውን መመስረቻ ጽሑፍ ለጉባኤው አቅርበው ጉባኤው ተወያይቶ እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል፡፡

ጠቅላላ ጉበኤውም የተሻሻለው የባንኩ መመስረቻ ፅሑፍ ላይ በጥልቀት በመወያየት ማሻሻያውን በሙሉ ድምፅ አፅድቆታል።

## 6.4 የጠቅላላ ጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

የጠቅላላ ጉባኤው ቃለ ጉባኤ ለባለአክሲዮኖች ተነቦ በሙሉ ድምፅ ፀድቋል።

## 7. ለጉባዔው የቀረቡ ሰነዶች

ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰነዶች ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ጋር ተያይዘዋል።

7.1 የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ፣

7.2 ባለአክሲዮኖች በቀድምትነት መብት አክሲዮን ለመግዛት ያላቸውን መብት በክፊል ለመገደብ ከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበ ሪፖርት

7.3 የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ የውጪ ኦዲተር ሪፖርት

7.4 የማህበሩ የተሻሻለ የመመስረቻ ፅሁፍ

## 8. የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የማህበሩ ፀሐፊ ማረጋገጫ

እኛ የእናት ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የማህበሩ ፀሐፊ በመስከረም 03 ቀን 2016 ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የተያዘው ቃለ-ጉባኤ በትክክል ስለመመዝገቡ በንግድ ህግ አንቀጽ 387(1) መሰረት በሙሉ ስምና ፊርማችን እናረጋግጣለን ።

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ ፍሬሕይወት ወርቁ በየነ | ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ ሀብቱ ድምፁ ወረስ | ም/ሰብሳቢ | |
| 3 | ወ/ሮ ሮማን ለገሰ ወ/ጊዮርጊስ | አባል | |
| 4 | አቶ ኢታና አያና ለታ | አባል | |
| 5 | ወ/ሮ ሽታዬ ሁሴን አህመድ | አባል | |
| 6 | አቶ እዮቤድ ጥበቡ ልሳነወርቅ | አባል | |
| 7 | ረ/ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ዉሂብ ወ/ማርያም | አባል | |
| 8 | ወ/ሮ ይርገዱ በጋሻው ሀብተየስ | አባል | |
| 9 | ወ/ሮ አዲስ ዘለቃው በለጠ | አባል | |
| 10 | ወ/ሮ ንግስት ወ/ስላሴ ገ/ኪሮስ | አባል | |
| 11 | አቶ አየነው ውዱ አዛገው | አባል | |
| 12 | ወ/ሮ ዕጌ ንጋቱ | የማህበሩ ፀሐፊ | |

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/፬ ጽ/ቤት አለ
ፊርማው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል።
ቁጥር ቀ8/00029 8/4/h/2016
5/4 2016

Zemenay Melesa Wube
Document Authentication
and Registration Expert IV

Documents Authentication & Registration Service Branch Office